Australian Government
Department of Social Services



# ጾታዊ ጥቃት

## አውስትራሊያ ውስጥ ማንኛውም ሰው ላይ ጾታዊ ጥቃት ማድረስ በህግ የተከለከለ ነው፡፡

የጾታ ጥቃት የሚፈጽም ማንኛውም ወንድም ሆነ ሴት እስር ቤት ሊገባ ይችላል፡፡

እርስዎ ወይም አንድ የሚያውቁት ሰው አደጋ ላይ እንደሆነ ካወቁ **000 ብለው** ፖሊስ ጋር ይደውሉ፡፡
የአውስትራሊያ ፖሊሶች ደህንነትን የሚያስጠብቁና ሊታመኑ የሚችሉ ናቸው፡፡

ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ነጻ የምክር አገልግሎትና መረጃ ለማግኘት በ**1800 737 732** ላይ 1800 RESPECT ብለው ይደውሉ፡፡

አስተርጓሚ በነጻ ማግኘት ከፈለጉ **131 450** ይደውሉ፡፡

## የአውስትራሊያ መንግስት (Australian Government) በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ጾታዊ ጥቃትን አይታገስም፡፡

ጾታዊ ጥቃት ካለግለሰቡ ስምምነትና ፈቃድ ውጪ በግለሰቡ ላይ የሚደረግ ጥቃት ነው፡፡

ጾታዊ ጥቃት የሚከተሉትን ሊጨምር ይችላል፡-

- አንድን ሰው ወሲብ ወይም ጾታዊ ድርጊቶችን እንዲፈጽም ማስገደድ፤
- ማንኛውንም ሰው ጾታዊ ምስሎችን እንዲመለከት ማስገደድ፤ ወይም
- ከህጻን ልጅ ጋር ወሲብ መፈጸም ወይም በጾታዊ ድርጊቶች መካፈል፤

በተጨማሪም በህይወት አጋር፣ በትዳር ጓደኛ ወይም በቤተሰብ አባል ላይ ጾታዊ ጥቃት ማድረስ ህገ-ወጥ ድርጊት ነው፡፡

## ሴቶችም ከወንዶች እኩል መብት አላቸው፡፡

የአውስትራሊያ ህግ ለወንዶችንም ሆነ ለሴቶች እኩል ይሰራል፡፡

እያንዳንዱ ሰው ደስተኛ በሆነ ግንኙነትና ማህበረሰብ ውስጥ ከጥቃት ነጻ የሆነ ህይወት የመኖር መብት አለው፡፡

ሴቶች በመጥፎ መንገድ ሲያዙ ወይም ጉዳት ሲደርስባቸው ሁኔታውን ዝም ብለው በጸጋ መቀበል የለባቸውም፡

## አውስትራሊያ ውስጥ፣ ባህል ላይ ያተኮሩ በዚህ ረገድ እርዳታ ሊሰጡ የሚችሉ አገልግሎቶች አሉ፡፡

**1800 RESPECT** የአውስትራሊያ ብሄራዊ ጾታዊ ጥቃት፣ የቤተሰብ እና የቤት ውስጥ ጥቃት የምክር አገልግሎት (Australia's National Sexual Assault, Family and Domestic Violence Counselling service) ሰጪ ነው፡፡ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ነፃ የስልክ እና የኦንላይን የምክር አገልግሎት እና መረጃ ይሰጣል፡፡ ምክር ሰጪዎቹ ያዳምጡዎታል፤ ጥያቄዎችዎን ይመልሳሉ እንዲሁም በአካባቢዎ ወደሚገኙ ሌሎች እገዛ ሰጪዎች ይመሩዎታል፡፡

በ**1800 737 732** ይደውሉ ወይም የ1800 RESPECT ድረ-ገጽን ይጎብኙ፡- **www.1800RESPECT.org.au**.

## አስተርጓሚ ያስፈልግዎታል?

የትርጉም እና የማስተርጎም አገልግሎት (**Translating and Interpreting Service)** (TIS)ን በስልክ ቁጥር **131 450** በነጻ ደውለው ያነጋግሩ፡፡ TIS ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር እንዲነጋገሩሊረዳዎት ይችላል፡፡ TIS የምክር አገልግሎት አይሰጥም፡፡